MCPS
ROCKVILLE, MARYLAND

# 2ኛ የውጤት መስጫ ክፍለጊዜ የ 5ኛ ክፍል የወላጆች መመሪያ

በማርክ መስጫ 2 ወቅት፣ የ5ኛ ክፍል ተማሪዎች ከዚህ በታች በተገለጸው ፅንሰ ሀሳቦችና ክህሎቶች ትምህርት ይቀበላሉ።
*እባክዎ ያስታዉሱ፡- በ ኢታሊክ የታዩት ችሎታዎች እና ጽንሰ-ሐሳቦች ትምህርት ተሰጥቷል ነገር ግን በሪፖርት ካርድ ላይ አልተመዘገበም።*

## ሂሳብ

በአስር ቤት ውስጥ ቁጥሮችና ግብረቶች/ስሌቶች

- ባለ-ብዙ-አሃዝ ሙሉ ቁጥሮች በመደበኛ የሂሳብ አሰራር/algorithm በቅልጥፍና ማባዛት።
- በቦታ ዋጋ በተመሰረቱ ስልቶች፣ የግብረቶች ጠባዮች፣ እና/ወይም በማባዛትና በማካፈል መካከል ባለው ዝምድና በመጠቀም፣ የእስከ አራት-አሃዝ ተከፋዮች እና የባለ-ሁለት-አሃዝ አካፋዮች ሙሉ-ቁጥር ውጤቶችን ፈልጎ ማግኘት።
- ስሌቱን በቀመሮች፣ በአራት ማእዘን ድርድሮች፣ እና/ወይም በስፋት ሞዴሎች በመጠቀም ስእል መስራትና ማብራራት።ቁጥሮች እና ግብረቶች ክፍልፋዮች
- የተሰጡ ክፍልፋዮችን በተመዛዛኝ ክፍልፋዮች በመተካት የማይመሳሰሉ ታህቶች/denominators (የተደባለቁ ቁጥሮችን ጨምሮ) ያሏቸውን ክፍልፋዮች መደመርና መቀነስ ተመዛዛኝ ድምር ወይም ተመሳሳይ ታህቶች ያሏቸው ክፍልፋዮች ልዩነት ውጤት በሚገኝበት ሁኔታ። ለምሳሌ፡- $\frac{2}{3}+\frac{5}{4}=\frac{8}{12}+\frac{15}{22}=\frac{23}{12}$.
(በአጠቃላይ፣ $\frac{a}{b}+\frac{c}{d}=\frac{(ad+bc)}{bd}$.)
- የክፍልፋዮች መደመርና መቀነስ የሚያካትቱ የቃል ፕሮብሌሞችን ወደ ተመሳሳይ ሙሉ በመምራት መፍታት፣ የማይመሳሰሉ ታህቶች ጉዳዮችን በማካተት፣ ለምሳሌ፣ ፕሮብሌሙን ለመወከል በሚታዩ የክፍልፋይ ሞዴሎች ወይም ቀመሮች መጠቀም። የመልሶችን ተቀባይነት በአእምሮ ለመገመትና ለመገምገም በክፍልፋዮች መመዘኛ እርከን እና በክፍልፋዮች የቁጥር አስተሳሰብ መጠቀም። ለምሳሌ፣ የተሳሳተ ውጤት ለይ፣ $\frac{2}{5}+\frac{1}{2}=\frac{3}{7}$ ያን በመመልከት{10}። $\frac{3}{7}<\frac{1}{2}$
- ኣንድን ክፍልፋይ ወይም ሙሉ ቁጥር በአንድ ክፍልፋይ ለማባዛት የማባዛት ተቀዳሚ ግንዛቤዎች መተግበር እና ማስፋፋት።
  - o (a/b) × q የሚለውን የማባዛት ውጤት q ወደ b እኩል የሆነ ክፍሎች ሲከፈል ኣንድ ከኣካሎቹ ብሎ መተርጎም ፤ በተመዛዛኝ መንገድ፣ የa × q ÷ b ግብረቶች ውጤት በመሆን። ለምሳሌ፣ (⅔) x 4 = (8/3)ን ለማሳየት በሚታይ በክፍልፋይ ሞዴል መጠቀም፣ እና ለዚህ ቀመር የታሪክ ኣውደንባብ መፍጠር። ⅔ x ⅘ = 8/15 ን በተመሳሳይ መስራት። ባጠቃላይ፣ (a/b) x (c/d) = (ac/bd)።
  - o ክፍልፋላዊ የጎን ርዝመቶች ያሉት ሬክታንግል/rectangleን ተገቢ የክፍልፋይ የጎን ርዝመቶች ባሏቸው ስኩዌርስ/squares በመደርደር/tiling ስፋቱን መፈለግ፣ እና ስፋቱ የጎን ርዝመቶችን በማባዛት ከሚገኘው ጋር እኩል ማሆኑን ማሳየት። የሬክታንግልስ ስፋቶች ለማግኘት ክፍልፋላዊ የጎን ርዝመቶችን ማባዛት፣ እና የክፍልፋል ውጤቶችን እንደ ሬክታንግላዊ ስፋቶች መወከል።
- ማባዛትን እንደ ማነፃፀሪያ ሚዛን (መጠን መለወጥ) መተርጎም፣ በ፡-
  - o ያንድን ብዜት ውጤት መጠን ከኣንድ ተባዥ መጠን ጋር በሌላው ተባዥ መጠን መሰረት ማወዳደር ፣ የተመለከተውን ማባዛት ሳያከናውኑ።
  - o የሆነ ቁጥርን ከ 1 በላይ ክፍልፋይ/ፍራክሽን ማባዛት የሚሰጠው ውጤት ለምን ከተሰጠው ቁጥር እንደሚበልጥ ማስረዳት (ከ1 ቁጥር በላይ በሆኑ ሙሉ ቁጥሮች ማባዛትን መደበኛ መሆኑን በመገንዘብ)፤ የሆነ ቁጥርን ከ 1 በታች ክፍልፋይ/ፍራክሽን ማባዛት የሚሰጠው ውጤት ለምን ከተሰጠው ቁጥር እንደሚያንስ ማስረዳት፤ እና የክፍልፋይ መርህ እኩልነት/አቻነት( equivalence ) a/b = (n x a)/(n x b)ን ከ a/b በ 1 የማባዛት ውጤት ጋር በማዛመድ።
- የክፍልፋዮችን እና የተደባለቁ ቁጥሮችን ብዜት በመጠቀም ተጨባጭ-ፕሮብሌሞችን ፍታ/ቺ።

## ምንባብ

ስለ ምንባብ መረዳት፡- ስነ ፅሁፍ

- ፅሁፉ በግልፅ የሚለውን ሲያብራሩ እና ከፅሁፉ መረጃ ሲወስዱ ከፅሁፉ በትክክል መጥቀስ።
- የኣንድ ታሪክ፣ ድራማ፣ ወይም ቅኔ ዘውግ ከፅሁፉ ዝርዝሮች መወሰን፣ በኣንድ ታሪክ ወይም ድራማ ገፀባህርያት ለፈተናዎች እንዴት ምላሽ እንደሚሰጡ ወይም በግጥም ወስጥ ተናጋሪ ኣንድ ርእስ ላይ እንዴት እንደሚያንፀባርቅ በማካተት፤ ፅሁፉን ማጠቃለል።
- በኣንድ ታሪክ ወይም ድራማ ሁለት ወይም ከዚያ በላይ ገፀባህርያት፣ ሁኔታዎች፣ ወይም ክውነቶችን ማወዳደርና ማነፃፀር፣ በፅሁፉ ውስጥ ከሚገኙ ልዩ ዝርዝሮች በመውሰድ።
- የተከታታይ ምእራፎች፣ ትእይንቶች፣ ወይም የግጥም ስንኞች እንዴት አንድ ላይ ተስማምተዉ የተለየ ፅሁፍን ኣጠቃላይ መዋቅር እንደሚሰጡ ማብራራት።
- የኣንድ ተራኪ ወይም ተናጋሪ ኣስተያየት ክውነቶች እንዴት እንደሚገለፁ ተፅእኖ እንደሚያደርግ መግለፅ።
- የሚታዩ እና ባለበርካታ-ሚድያ ንጥረነገሮች ለኣንድ ፅሁፍ ትርጉም፣ ቃና፣ ወይም ውበት እንዴት እንደሚያበረክቱ መተንተን።
- በተመሣሣይ ፍሬ ነገሮች እና ርእሶች ላይ የተነገሩ ታሪኮችን ስለአቀራረባቸው እያነፃፀርክ/ሽ አወዳድር/ሪ።
- በ5ኛ ክፍል ደረጃ በሚገባ ውስብስብ የሆነ ስነ-ጽሑፍን ኣንብቦ መገንዘብ።
ስለ ምንባብ መረዳት፡- መረጃያዊ
- ፅሁፉ በግልፅ የሚለውን ሲያብራሩ እና ከፅሁፉ መረጃ ሲወስዱ ከፅሁፉ በትክክል መጥቀስ።
- የኣንድን ፅሁፍ ሁለት ወይም ከዚያ በላይ ዋነኛ ኣስተሳሰቦች መወሰን እና በቁልፍ ዝርዝሮች እንዴት እንደሚደገፉ ማብራራት፤ ፅሁፉን ማጠቃለል።
- በኣንድ ታሪካዊ፣ ሳይንሳዊ፣ ወይም ቴክኒካዊ ፅሁፍ ውስጥ የተለየ መረጃ ላይ የተመሰረተ በሁለት ወይም ከዚያ በላይ ግለሰቦች፣ ክውነቶች፣ ኣስተሳሰቦች፣ ወይም ፅንሰሃሳቦች መካከል የሚገኙ ዝምድናዎችን ወይም ግንኙነቶችን ማብራራት።
- በጽሑፉ ውስጥ አጠቃላይ የአካዳሚክ እና በጎራ-የተወሰኑ ቃላት እና ሀረጎችን ትርጉም ለይተህ(ሽ) ግለጽ(ጪ)።
- ከሁለት ወይም ከዚያ በላይ ጽሑፍ ላይ አጠቃላይ የድርጊቱን ቅንብር፣ ሃሳቦችን፣ ፅንሰሃሳቡቹን፣ ወይም መረጃ/ኢንፎርሜሽን አወዳደር/ሪ እና አነፃጽር/ሪ።
- በሚወክሉት ኣስተያየት ውስጥ ኣስፈላጊ ተመሳሳይነቶችንና ልዩነቶችን እያመላከቱ፣የተመሳሳይ ክውነት ወይም ርእስ በርካታ ትረካዎችን መተንተን።
- ለጥያቄ በፍጥነት/ቶሎ መልስ የማግኘት፣ ወይም ችግርን/ፕሮብሌምን በብቃት የማቃለል ችሎታህ(ሽ)ን ለማሳየት ከተለያዩ ህትመቶች ወይም ዲጂታል ምንጮች መረጃ/ኢንፎርሜሽን አግኝ/ኚ።
- አንድ ደራሲ በአንድ ጽሑፍ ውስጥ ያሉ ነጥቦቹን ለመደገፍ እንዴት ማስረጃዎችን እና ማስረጃዎችን እንደሚጠቀም/እንደምትጠቀም የትኞቹ ምክንያቶችና ማስረጃዎች የትኛውን ነጥብ እንደሚደገፉ ጭምር አብራራ(ሪ)።
- በአርእስቱ ላይ በእዉቀት መፃፍ ወይም መናገር እንዲቻል ከተለያዩ ፅሁፎች በተመሳሳይ ርእስ መረጃ ማዋሐድ።
- ለ5ኛ ክፍል በኣግባቡ ውስብስብ የሆኑ መረጃያዊ ፅሁፎችን ማንበብ እና መገንዘብ።

ቋንቋ፡- የቃላት እውቀትና አጠቃቀም

- በ5ኛ ክፍል ርእሶችና ፅሁፎች በትብብሮሽ ውይይት መስክ በውጤታማነት መሳተፍ፣ በሌሎች አስተሳሰቦች ላይ በመገንባት እና የግልን በጥራት እየገለፁ።
- ድምፅ ከፍ ተደርጎ የተነበበ የተጻፈ ፅሁፍን ወይም በተለያዩ ሚድያና፣ በሚታይ፣ የብዛት/መጠን እና የቃልን በሚያካትቱ ቅርፀቶች የቀረበ መረጃን ማጠቃለል።
- በ5ኛ ክፍል ምንባብ በመመስረት ያልታወቁና ባለ-በርካታ-ትርጉም ቃላቶችንና ሃረጎችን ትርጉም መወሰን ወይም ማብራራት።
- የዘይቤያዊ አነጋገር፣ የቃል ዝምድና፣ እና በቃል ትርጉሞች ውስጥ የሸሙጦችን ግንዛቤ ማሳየት።
- የክፍል-ተገቢ አጠቃላይ አካዴሚያዊና ባለ-ልዩ-መስክ ቃላቶችና ሃረጎች፣ ንፅፅር፣ መደመር፣ እና ሌሎች ሎጂካዊ ዝምድናዎችን (ለምሳሌ፣ የሆነ ሆኖ፣ ምንም እንኳን፣ ቢሆንም፣ በተመሳሳይ፣ በተጨማሪ) የሚያካትቱ ማወቅ/ማግኘትና በትክክል አገልግሎት ላይ ማዋል።

## ጽሑፍ

ትምህርት ሰጭ/ገላጭ

- አንድን ርእስ ለማገናዘብና እስተያየቶችንና መረጃዎችን በግልፅ ለማስተላለፍ መረጃያዊ/ገላጭ ፅሁፎች መፃፍ።
- አንድ ርእስ በግልፅ ማስተዋወቅ፣ አጠቃላይ ትዝብት እና ትኩረት መስጠት፣ ርእሱን በሃቆች፣ ፍቺዎች፣ ጭብጥ ዝርዝሮች፣ ጥቅሶች፣ እና ከቡድን ጋር በተዛመዱ መረጃዎች በሎጂክ ማዳበር፣ ቅርፀት (ለምሳሌ፣ አርእስቶች)፣ ስእሎች፣ እና በርካታ-ሚድያ ግንዛቤን ለማገዝ ጠቃሚ ሲሆን ማካተት።
- አርእስቱን ለማስተዋወቅ ወይም ለመግለጽ ትክክለኛውን ቋንቋ እና የድርጊቱን-ቃላት ተጠቀም/ሚ።
- ከቀረበው መረጃ ወይም ማብራርያ ጋር የተዛመደ ማጠቃለያ አረፍተሃሳብ ወይም ክፍል ማቅረብ።

ትረካ

- እውነተኛ ወይም ሃሳብ የወለዳቸው ተሞክሮዎችን ወይም ክውነቶችን ለማዳበር ውጤታማ ቴክኒክ፣ ገላጭ ዝርዝሮች፣ እና በጠሩ የክነት ቅደም-ተከተሎች በመጠቀም ትረካዎችን መጻፍ።
- ተሞክሮዎችንና ክውነቶችን ለማዳበር ወይም የገፀባህርያትን ምላሾች ለሁኔታዎች ለማሳየት፣ ውይይት፣ ገለፃ፣ እና እርምጃ በመሳሰሉ የትረካ ቴክንኮች መጠቀም።
- የተለያዩ የክስተቶችን/የክውነቶችን ቅደም ተከተሎች ለመቆጣጠር በተለያዩ የሽግግር ቃላት፣ ሃረጎች እና አንቀፆች መገልገል።
- ከተተረኩ ተሞክሮዎች ወይም ክውነቶች የሚከተል አንድ መደምደሚያ ማቅረብ።

አስተያየት

- በርእሶች ወይም በፅሁፎች ላይ በምክንያቶችና በመረጃዎች እየደገፉ የአመለካከት አጫጭር ድርሰቶችን አስተያየት ፃፍ/ፊ።
- አንድ ርእስ ወይም ፅሁፍን በጥራት ማስተዋወቅ፣ እስተያየት ማቅመጥ፣ እና አስተያየቶች በሃቆችና በዝርዝሮች የተደገፉበት፣ እና የፀሃፊው(ዋ)ን ኣላማ ለመደገፍ በሎጂክ የተመደቡበት ድርጅታዊ መዋቅር መፍጠር።
- በቃላቶች፣ ሃረጎች፣ እና በአንቀፆች (ለምሳሌ፣ በተከታይ፣ በተለይ) በመጠቀም አስተሳሰብንና ምክንያቶችን ማገናኘት።
- ከቀረበው ሃሳብ ጋር የሚገናኝ ማጠቃለያ/የመደምደሚያ ሃሳብ መግለጫ ስጥ/ጪ። ሂደት፣ ውጤት፣ ጥናት/ምርምር
- እድገቱና አደረጃጀቱ ለተግባር፣ ኣላማ፣ እና ለአድማጭ ተገቢ የሆነ ጥራት ያለውና ስሙሙ ፅሁፍ ማቅረብ።
- ከእኩዮችና ከአውቂዎች አመራርና ድጋፍ ጋር፣ ፕላን፣ ክለሳ፣ አርትኦ፣ ዳግመ-ፅሁፍ፣ ወይም አዳዲስ ሙከራ እንደአስፈላጊነቱ በማድረግ፣ ፅሁፍን ማዳበርና ማጠናከር።
- መረጃዎችን በማስታወሻዎች እና ባለቀ ስራ ማጠቃለል ወይም በሌላ ኣባባል ማስቀመጥ፣ እናም የምንጮች ዝርዝር ማቅረብ።
- ትንተና፣ አስተሳሰብ፣ እና ምርመራን ለመደገፍ ከስነፅሁፍ ወይም ከመረጂያዊ ፅሁፎች ማስረጃ መውሰድ።
- ለተለያዩ ዲስፒሊን-ተኮር ተግባሮች፣ ኣላማዎች፣ እና ታዳሚዎች በተራዘም የጊዜ መቃኖች/ማዕቀፎች እና አጫጭር የጊዜ መቃኖች/ማዕቀፎች በድግግሞሽ መፃፍ። የቋንቋ አጠቃቀም

- አንድ ርእስ ላይ ወይም ጽሑፍ ላይ ሪፖርት ወይም አስተያየት አቅርብ/ቢ፣ የሃሳቦችን ቅደምተከተል በመጠበቅ እና ተጨባጭነታቸውን እና ዋና ዋና ሃሳቦችን ወይም መሪ ሃሳቦችን በተገቢ ዝርዝር በማስደገፍ ለመረዳት በሚያስችል ሁኔታ ተናገር/ሪ።
- አስፈላጊ ሲሆን ዋናውን ሃሳብ ወይም ፍሬ ነገሩን ለማዳበር መገናኛ ብዙሃን መገልገያዎችን እና በዓይን የሚታዩ ነገሮችን ጨምረህ/ሽ አቅርብ/ቢ።
- እንግሊዘኛን ሲፅፉ ወይም ሲናገሩ ደረጃውን የጠበቀ የእንግሊዘኛ ሰዋስው እና አጠቃቀም። እና ሲፅፉ ካፒታላይዜሽን፣ ስርአተነጥብ፣ እና የፊደል አመራረጥ ችሎታ ማሳየት።
- ለትርጉም፣ ለአንባቢ/አድማጭ ፍላጎት፣ እና ለዘየ አረፍተነገሮችን ማስፋፋት መገጣጠም፣ እና መቀነስ።

## ሳይንስ

መሬትና የህዋ ሳይንሶች

- መረጃ/ኢንፎርሜሽን ለማስተላለፍ ቅጦች/ቅደምተከተሎች የሚጠቀሙ በርካታ መፍትሔዎችን ፍጠር(ሪ) እና አነፃፅር(ሪ)።
- ቅርፀቶችን በመጠን እና በሞገድ ርዝመት ለመግለፅ እና ማእበሎች ነገሮችን እንዲንቀሳቀሱ ምክንያት ሊሆኑ እንደሚችሉ የማእበሎች ሞዴል ማዳበር።
- ከአንድ ቁስ አካል የሚያንፀባርቅ ብርሃን ወደ ዓይን ሲገባ/ሲያንፀባርቅ ቁስ አካሉ እንዳይታይ እንደሚያደርግ ናሙና አዘጋጅተህ(ሽ) አስረዳ(ጂ)።
- በቁስ አካላት ላይ መሬት የምትጠቀመው የስበት ኃይል ወደታች/ቁልቁል ይስባል የሚለውን ክርክር የሚደግፍ ሃሳብ ስጥ(ጪ)።
- በቁስ አካላት ላይ መሬት የምትጠቀመው የስበት ኃይል ወደታች/ቁልቁል ይስባል የሚለውን ክርክር የሚደግፍ ሃሳብ ስጥ(ጪ)። ምህንድስና ንድፍ እና ሂደት
- አንድን ችግር/ፕሮብሌም እና የችግሩን ይዘት/ውስብስብነት ጭምር በተቻለ መጠን ለመፍታት የሚያስችል መመዘኛ እና የተለያዩ መፍትሔዎችን በማወዳደር/በማነፃፀር ለእያንዳንዱ መፍትሔዎችን አፍልቅ(ቂ)።
- ለስኬታማነት የተወሰነ መስፈርትን እና የቁስ፣ የጊዜ፣ እና የወጪ ገደብን ያካተተ አንድ ፍላጎትን ወይም መሻትን የሚያንጸባርቅ ቀላል ንድፍ ፕሮብሌም መግለጽ።

## ማህበራዊ ጥናቶች

የስነ-ዜጋ ትምህርት

- ግለሰቦችና ቡድኖች ለሜሪላንድ የፖለቲካ ስርኣት እንዴት አስተዋፅኦ እንዳደረጉ መተንተን።
- በሜሪላንድ መንግስት የግለሰቦችንና የቡድኖችን መብቶች እንዴት እንደሚከላከል መግለፅ።
- የመንግስትን ቀደምት መሰረቶች፣ ተግባሮች፣ እና ኣላማዎች ማገናዘብ።
- የፖለቲካዊ ስርኣቶቻችን መሰረቶች የሆኑትን ታሪካዊ ክውነቶች፣ ሰነዶች፣ እና ልምዶች መተንተን።
- ህዝባዊ መመርያና ጉዳዮችን በሚመለከት የቅኝ ግዛት መንግስትን ሚናዎች መተንተን።
- የግለሰብ ሚናዎችና አስተያየቶች የኣሜሪካን ፖለቲካዊ ስርኣት እንዴት እንደሚቀርፁ መተንተን።
- እንደ የዩናይትድ ስቴትስ ዜጋ የሲቪል ተሳትፎን አስፈላጊነት መተንተን።
- በአሜሪካ (ዩ.ኤስ) ውስጥ ስለ መብቶች እና ኃላፊነቶች አብራራ(ሪ)።
- የህጋዊነት መርህ ማገናዘብ። ባህል
- የሜሪላንድ ሰዎችን እይታ/አመለካከት ገምግም(ሚ)።
- በቅኝ ግዛት ዘመን የነበሩ የግንኙነት ምክንያቶችን ተንትን/ኚ።ታሪክ
- የአሜሪካን ርዕዮት የፈጠረውን/ያስከተለውን ተፅእኖ ተንትን(ኚ) በዝርዝር አስቀምጥ(ጪ)።

## መረጃዊ/ኢንፎርሜሽናል ማንበብ እና መጻፍ

- የመረጃ ፍላጎትን ለማሟላት የሚያስችሉ ጥያቄዎችን ፍጠር/ሪ።
- ተፈላጊ መረጃ ለማሟላት መገልገያዎችን መለየት።
- ተፈላጊ መረጃን ለማሟላት የተቀረፀ/የተመዘገበ ውሂብ/መረጃ ጥራት መገምገም እና መተንተን።
- የመረጃ ፍላጎትን ለማሟላት ምንጮችን መርምር(ሪ)/ምረጥ(ጪ)።
- ኣሃዞችን/መረጃዎችን በተለያዩ ቅርፀቶች መመዝገብ።
- የመረጃውን ግኝቶች/መደምደሚያዎች ለማዘጋጀት የተለያዩ ቅርፀቶችን ተጠቀም/ሚ።
- የምንጩን ዝርዝር ለመፍጠር ተቀባይነት ያለውን ዋቢ ተጠቀም/ሚ።

## ስነጥበብ

ኪነትን መፍጠርና ከኪነት ጋር ግንኙነት

- ለስነጥበብ ሥራ የፈጠራ መፍትሔዎችን ለማፍለቅ ሃሳቦችን አጠናቅር(ሪ)።
- ሃሳብን፣ ስርአተ ሒደት፣ ወይም ውጤት ለማስተላለፍ፣ የስነጥበብ መሠረታዊ ንጥረነገሮችን እና የንድፍ መርሆችን ተጠቀም(ሚ)።
- የእደጥበብ መሥሪያዎችን፣ ሚዲያ፣ እና የሥራ ቦታን ሲጠቀሙ ተገቢውን የሥነጥበብ መሥሪያ ዘዴዎችን/ቴክኒኮችን እና ሥርአቶችን ይምረጡ።
- የእደጥበብ ሥራን ትርጉም ለማዳበር እና የእጅ ሙያን ለማሻሻል ግብረመልስ/ምላሽ አስተያየትን ተግባራዊ አድርግ(ጊ)።
- ለለውጥ ምላሽ  የኪነጥበብ ስራ ይፍጠሩ።
- እምነትን፣ እሴትን፣ ወይም ባህርይን ለመለወጥ ስነጥበብ እንዴት እንደሚጠቅም አስረዳ(ጂ)። የኪነጥበብ አቀራረብ እና የኪነጥበብ ግብረመልስ
- የሥነጥበብ ሥራን በመምረጥ በአርቲስቱ አገላለጽ መሠረት እንዴት የአውደርዕይ መስፈርት እንደሚያሟላ ግለጽ(ጪ)።
- የእደጥበብ ሥራን በተለየ የአውደርዕይ/የኤግዚቢሽን ስፍራ/ቦታ ለማቅረብ አመቺ/ተገቢ ዘዴዎችን ተግባራዊ አድርግ(ጊ)።
- ከጊዜ ወደ ጊዜ የእደጥበብ ሥራ እንዴት እየተለወጠ እንደሄደ የሚያሳዩ በግል የተሰበሰቡ የስነጥበብ ውጤቶችን አስረዳ(ጂ)።
- በአንክሮ መከታተል/ማስተዋል የስነጥበብ ስራዎችን ትንተና እንዴት እንደሚለወጡ አብራራ/ሪ።
- በግል የታቀደ የስነጥበብ ሥራ ግቡን መትቶ እንደሆነ ለማረጋገጥ መስፈርት መርጠህ(ሽ) ተጠቀም(ሚ)።

## ሙዚቃ

የሙዚቃ ዝንባሌ/ምላሽ መስጠት

- ከተለያዩ ባህሎች ሙዚቃ ውስጥ ሙዚቃዊ ፎርም መግለፅ።
- በጆሮ ሲቀርብ የኣንድን የሙዚቃ ክፍል ሞድ ሜጀር ወይም ማይነር መሆኑን መለየት።
- የሙዚቃ ንጥረነገሮች ለተለያዩ የኣለም ባህሎች በጆሮ ናሙናዎች እንዴት ኣገልግሎት ላይ እንደሚውሉ መግለፅ።
- መስፈርቶችን ማዳበር እና የራሳቸውን እና የሌሎችን ኣፈፃፀም ለመገምገም ተግባራዊ ማድረግ። ሙዚቃ መጫወት
- ከፍ ባለ ድምፃዊ ኣገላለፅ/አወጣጥና በግልፅ ቋንቋ እና የዳድ/ከአጋር ጋር ጣእመ ዜማ ያላቸውን መዝሙሮች በትክክል መዘመር።
- ሌሎች ተማሪዎች ሲዘምሩ ወይ ንፅፅራዊ ድርሻዎችን ሲጫወቱ፣ ቀላል የክር ኣጃቢዎችን ማቅረብ።
- በቡድኖች ውስጥ ሆኖ መዘመር፣ ተምቡሮችን በመደባለቅ እና ዳይናሚክ ደረጃዎችን በማጋጠም።
- ባህላዊ ዘፈን እና ባህላዊ ጭፈራዎችን ከተለያዩ የኣለም ባህሎች ማቅረብ።
- ከተለያዩ ታሪካዊ ወቅቶች እና ከኣለም ባህሎች፣ የተወሰኑ ከኣጠቃላይ የመማርያ ክፍል ጥናቶች ጋር የተያያዙትን ጨምሮ፣ ዘፈኖችን/መዝሙሮችን እና ዳንሶችን ማቅረብ።

የሙዚቃ ንባብና ፅሁፍ/ቅኝት

- እንድ ቀላል ዜማ በትሬብል ስታፍ በተለያዩ ቁልፎች በሶልፌጅዮ ወይም በተመጣጣኝ ስርኣት ማንበብና መጫወት።
- ሚዛኑን በጠበቀ ኖታ በመጠቀም ኣንድ ኣጭር ዜማዊ ሃረግ ከቃል ፅሁፍ ኖታ መውሰድ። የሙዚቃ ፈጠራ
- ለክፍል ውስጥ መሣሪያዎች ጣዕመዜማ አዘጋጅ*(ጂ)*።

## የአካል ማጠንከርያ ትምህርት

የግልና የማህበራዊ ሃላፊነት

- ለበለጥ ግኝት ግስጋሴን እየተቆጣጠሩ የግል እንቅስቃሴ ግቦችን መመስረትና ማሻሻል።
- የጊዜ ኣስተዳደር ስልቶችን በብልሃት መተግበር። የእንቅስቃሴ ክህሎቶች እና እሳቤዎች
- የራስ-በራስ-መገምገም እና ግብረመልስ በመንቀሳቀስ ክሂሎቶች መሻሻል ኣስፈላጊነታቸውን ማወቅ።
- በስተላይ-የተወረወረን ነገር መያዝ ማሳየት።
- በመያዝ፣ መግፋት፣ እና መወርወር ላይ የሚያስፈልጉ ክሂሎቶችን ማጣራት።
- በኣካል ክፍሎችና በመሳርያዎች ለመምታት ተፈላጊ ክሂሎቶችን ማሻሻል።

## የጤና ትምህርት

ስለ ግል እና የሸማች/የተጠቃሚ ጤንነት *(PCH)*

- ለደህንነት፣ ለበለጠ ጤናማ ህይወቶች የጤና ኣደጋዎችን ለመቀነስ ጤና-ኣራማጅ/የሚያጎለብቱ ስነምግባሮችን መለየትና መለማመድ።
- በሸማች የጤና ችግሮች እና አገልግሎቶች ላይ ስለ ጤንነት መረጃ/ኢንፎርሜሽን የሚሰጡ መርጃዎችን ጠቁም/ሚ። ደህንነትና ጉዳት
- ወደ ዉስጥ ዓየር በመሳብ ያለአግባብ የሚወሰዱ የቤት ውስጥ ምርቶችን ለይ።
- ፆታዊ ወከባን እንደ ሁከት አይነት እውቅና መስጠት።